# አትበል እሹሩሩ

የሀገር መመኪያ ፣ ደጀን ባላደራ
በደም በአጥንቱ ፣ ኢትዮጵያን ያኮራ
እንደሻማ ቀልጦ ፣ ለሃገር ያበራ
ዋልታና ምሰሶ ፣ ያንድነት ደመራ
ኢትዮጵያ እምንላት ፣ አገርን የሰራ
ማለቂያ የሌለው ፣ ተጭኖት መከራ
አማራን ማሳደድ ፣ ተይዞ ምንጠራ
ከምስራቅ ከምዕራብ ፣ ከደቡብ ሲጣራ
ጀሮ ዳባ ያለው ፣ ምን ነካው አማራ ።

ለመሞት ሳይሳሳ ፣ ለወገኑ ደምቶ
ላገር ለድንበሩ ፣ ተዋድቆ ተዋግቶ
አጥንቱን ከስክሶ ፣ በጀግንነት ሞቶ
ኢትዮጵያን ባቆመ ፣ ለዘመናት ተግቶ
ስራና ታሪኩ ፣ ውለታው ተረስቶ
ከኖረበት ስፍራ ፣ ከቀዬው ተገፍቶ
በግፍ በጭካኔ ፣ አይሞቱ ሞት ሞቶ
ለዚህ ወገን ደራሽ ፣ እንዴት ይጥፋ ከቶ
አማራውን ፈጁት ፣ አማራው ተኙቶ ።

ምን ይሆን ሚስጥሩ ፣ አማራ አይቆጣ
ወገኑን ሲታደግ ፣ ሆ! ብሎ እማይወጣ?
አልሰማ አለው ወይ ፣ ጥቃት የወገኑ
ዋይታውና ለቅሶው ፣ ስቃይና ሃዘኑ
ምን ነካው አማራ ፣ አይገለጥ አይኑ ።

ኧረ እኮ ምን ነካው ፣ እኔን ግራ ገባኝ
መከራና ግፉን ፣ እንዴት አይልም በቃኝ
የጭካኔን ገደብ ፣ ዳር ጥጉን ሲያሳዩት
በየ ጉራንጉሩ ፣ ዘቅዝቀው ሲሰቅሉት
አሳደው ከገደል ፣ ገፍትረው ሲጥሉት
ያለ ርህራሄ ፣ በቁም ሲያቃጥሉት
ያስከሬንን ተራራ ፣ አርገው ሲቆልሉት
ምነው አማራውን ፣ ምን ነካህ አትሉት ?

አልገባኝም ጭራሽ ፣ የአማራ ሚስጥሩ
መቼ ነው የሚፈርስ ፣ የትግስት አጥሩ
ድፍርስርስ ካላለ ፣ መች ይጠጣል ጥሩ
እስኪ ሞረሽ ሞረሽ ፣ በሉና ተጣሩ
በገጠር ከተማው ፣ ጭንቅ ይሁን ምድሩ
የጠላትህ መግቢያ ፣ ይማስ መቃብሩ
ጠላት ወዳጅ ላይሆን ፣ አትበል እሹሩሩ ።

ታዛቢው

May 22, 2018